# ግልጽ ደብዳቤ ለኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ

**ለአቶ መለስ ዜናዊ**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ**
**ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**
**<u>አዲስ አበባ ፣ ኢትዮጵያ</u>**

**ነሐሴ** 2 **ቀን** 1999 **ዓ.ም.**

**ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ፤**

**ሀገራችን ኢትዮጵያ ሉዓላዊነቷንና የግዛት አንድነቷን ጠብቃ ለዘመናት የኖረች ሀገር በመሆኗ ፤ በቅኝ ግዛት ቀንበር ለነበሩ ሀገሮች የነፃነት ጮራ ፈንጣቂ እየተባለች በመጠቀስ በታሪክ ከፍተኛ ሥፍራ ይዛ የቆየች ሀገር ናት።**

**ኢትዮጵያ በሺህ ዓመታት በሚቆጠር የታሪክ ዘመኗ የግዛቷ ሥፋት አሁን ካለዉ እጅግ በጣም የሠፋና የንግድ ግንኙነቷም ከደንበርተኛዋ ኑቢያ ማዕከል ድረስ ይዘልቅ እንደነበር የእኛ ታሪክ ፀሐፊዎች ብቻ ሳይሆኑ የዉጭ ሀገር ጠበብቶች የመዘገቡት ታሪክ ነው።**

**በሀገራቸን ተፈጥሮአዊ አቀማመጥ በተለይም በአባይ ወንዝና እሰከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በነበራት የባሕር በር ሳቢያ ከኦቶማን ቱርክ ፣ ከግብጽ ፣ ከኢጣልያንና ከድርቡሽ ወራሪዎች ጋር በየዘመናቱ በተደጋጋሚ ከፍተኛ መስዋዕትነት የተከፈለባችዉ በርካታ ጦርነቶች ተካሂደዋል።**

**በዚህ ረገድ የኢሕአዴግ መንግሥት ሥልጣን ከመያዙ በፊት ሀገራችንን ያስተዳድሩ የነበሩት መንግሥታት በአስተዳደር ብልሹነት ፣ ለግል ጥቅምና ዝና በመሻት ረገድ ይወቀሱና ይጠየቁ እንደሆነ እንጂ ፤ የሀገራችን ሉዓላዊነትና ዳር ድንበርን በማስከበርና የኢትዮጵያን ሕልዉና በማስጠበቅ ረገድ ታግለዉ ያታገሉ መሆናቸዉን የታሪክ ገድላቸዉ ሕያው ምስክር ነው።**

**ይህ በሕዝቧ ተጋድሎና መስዋዕትነት ለዘመናት ተከብሮ የኖረዉ የግዛት አንድነት ፤ ዛሬም ጠብቆ የማቆየትና ለተተኪዉ ትዉልድ የማስተላለፍ ኃላፊነት ለአሁኑ ትዉልድ የተጣለ ታሪካዊ አደራ መሆኑ ግልጽ ነዉ።**

**ሰሞኑን በአንዳንድ ዓለም አቀፍ የዜና ተቋሞች ኢትዮጵያ ከሱዳን ጋር በረጅሙ በሚያዋስናት ሰሜን ምዕራብ የግዛት ወሰን አስመልክተው ለሱዳን መሰጠቱን ዘግበዋል። በዋቢነት ለመጥቀስ ያህል ሱዳን ትሪቢዩን** ( Sudan Tribune ) **የተባለዉ የሱዳን ዜና አዉታር እ.አ.አ.** July 4, 2007 " Eastern Sudan Farmers get back Disputed Lands from Ethiopia " **በሚል ርዕስ ባወጣዉ ዜና የምሥራቅ ሱዳን አል-ገዳሪፍ ክፍለ-ሀገር ገዥ የሆኑትን አብደልራህማን አል-ከዲርን በመጥቀስ « የመሬቱን ርክክብ የሚያስፈጽሙ ሰባት ሰባት ሰዎች ያሉት ኮሚቴ ከሁለቱም ወገን የተዉጣጣ መሆኑንና ርክክቡን አስመልክቶ ቴክኒካዊ ዝግጅቱ መጠናቀቁን » መናገራቸውን ገልጿል። ይኸዉ የዜና አዉታር በሁለቱ ሀገሮች ወሰን የሚገኘው ለም የኢትዮጵያ የእርሻ መሬት ለ**17 **የሱዳን መንደር ነዋሪዎች መሰጠቱን የዘገበዉ ዜና ፤ ላለፉት** 16 **ዓመታት ይህን የሀገራችን የግዛት ክልል አስመልክቶ ይሰራጭ ከነበረው ስጋት ጋር ተዳምሮ ማንኛዉንም ኢትዮጵያዊ እጅግ ያስደነገጠና ያሳሰበ ጉዳይ ሁኗል።**

በተለይም በተፈጠረዉ አጋጣሚ ሱዳናዉያን ተጠቃሚ ሲሆኑ ፤ በዚህ የሀገራችን የወሰን ክልል ለዘመናት የኖሩ ኢትዮጵያዉያን ወገኖቻችን ከእርሻ መሬታቸዉና ከመንደሮቻቸዉ ተፈናቅለዉ ለክፉ ችግርና ለስደት ተዳርገዉ እንደሚገኙ አንዳንድ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

የኢሕአዴግ መንግሥት የሀገርን የግዛት ወሰን አሳልፎ ለጎረቤት ሀገር ሰጠ ተብሎ በሰፊዉ በሚነገርበት በአሁኑ ወቅትና እንዲህ ያለ የሀገር ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት በሚመለከት ዓብይ ጉዳይ ላይ አዉንታዊ ይሁን አሉታዊ መልስ በመስጠት ሕዝቡ በይፋ እንዲያዉቀዉ በመንግሥት በኩል የተደረገ ጥረት ባለመኖሩ ሁኔታዉ እጅግ አሳሳቢ እንዲሆን አድርጎታል።

ይህ ጉዳይ ማንኛዉንም የሀገሪቱ ዜጋ ሁሉ የሚያሳስብ ፣ የሚመለከተዉና ነቅቶ የሚጠብቀዉ ከፍተኛ ጉዳይ በመሆኑ በመንግሥት በኩል ተገቢ ማብራሪያ ሊያገኝ ይገባዋል።

ስለዚህ እርስዎ በአለብዎት መንግሥታዊ ኃላፊነት ከሱዳን ጋር በሚያዋስነዉ የሰሜን ምዕራብ የኢትዮጵያ የግዛት ወሰንን በሚመለከት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግልጽና ይፋ መግለጫ እንዲሰጡበት በማክበር እንጠይቃለን።

ከአክብሮት ጋር ፤

ጉዳዩን በከፍተኛ ትኩረት
የሚከታተሉ ኢትዮጵያዉያን

<u>ግልባጭ</u> -

1. ለኢትዮጵያ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
   <u>አዲስ አበባ ፣ ኢትዮጵያ</u>

2. ለአማራ ክልል መስተዳድር
   <u>ባሕር ዳር ፣ ኢትዮጵያ</u>

3. ለቤንሻንጉል-ጉሙዝ ክልል መስተዳድር
   <u>አሶሳ ፣ ኢትዮጵያ</u>

4. ለሰሜን ጎንደር መስተዳድር
   <u>ጎንደር ፣ ኢትዮጵያ</u>

5. ለደቡብ ጎንደር መስተዳድር
   <u>ደብረታቦር ፣ ኢትዮጵያ</u>

6. ለሁሉም ተቃዋሚ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ድርጅቶች